Association of Ethiopians in Europe
የኢትዮጵያውያን ማህበር በአዉሮፓ
www.ethiodiaspora.net

# ከኢትዮጲያዊያን ማሕበር በአውሮፓ የተላለፈ አስቸኳይ መግለጫ

August 5-2023

## ለተከበርከው ውድ የአማራ ሕዝብ ሆይ፡-

በይልቃል ከፋለ (ዶ/ር) የሚመራው የአማራ ብልጽግና ሐሙስ አገስት 3 ቀን 2023 ዓ ም ባወጣው መግለጫ በፋሺስቱ ኦነጋዊው የኦህዴድ ቡድን የሚመራውን የፌዴራል መንግስት ቡድንን ከአማራ ክልል ምክር ቤት ጋር ሳይመካከር ወደ አማራ ክልል ገብታችሁ ህዝቤን ጨፍጭፉልኝ ብሎ ጥሪ ማቅረቡ ይታወቃል።

ይህ በይልቃል ከፋለ የተላለፈው ጥሪ እመራዋለሁ በሚለው ሕዝብ ላይ ግልጽ የጭፍጨፋ ዘመቻን የማወጅ መሆኑን እኛ በአውሮፓ በአፍሪካና በመካከለኛው ምስራቅ የምንኖር ኢትዮጲያዊያን በጽኑ አምነናል።

ይልቃል ከፋለ ጨፍጫፊውን እና ኦነጋዊውን የኦህዴድ ሰራዊት ባለፈው ሚያዚያ ወር ላይ የክልሉን ልዩ ኋይል የመበትን ውሳኔን ካስተላለፈ በኋላ ወደ አማራ ግዛት እንዲገባና በሺህ የሚቆጠሩ ንጹሃኖችን እንዲጨፈጭፍ ፍቃድ በሰጠ አምስተኛ ወር ላይ ዛሬ አገስት 3 ቀን 2023 ባደረገው አዲስ ተጨማሪ የፌዴራል መንግስት ተብዬውን ጥሪ ቡድኑ - ማለትም በይልቃል የሚመራው የአማራ ብልጽግና ሙሉ በሙሉ መፍረሱንና ብሎም በሕዝባችን ላይ መጠነ ሰፊ የጭፍጨፋን አዋጅ ያወጀ መሆኑን ያረጋገጠበት ጥሪ ሆኖ ነው የምናየው።

ስለሆነም ዶ/ር ይልቃል ከፋለና ግብረ አበሮቹ የአማራ ብልጽግና የሚባለው ጸረ አማራው ብአዴን ላንዴና ለመጨረሻ ግዜ በአማራ ሕዝብና በአማራ ግዛት ላይ አንዳችም የሆነ ምድራዊ ሕግ ሞራላዊና ብሎም መንፈሳዊ ስልጣንና ኋላፊነት የሌለው መሆኑን መላው የአማራ ሕዝብና ብሎም የተቀረው መላው የኢትዮጲያ ሕዝብ በአጽንኦት ማወቅ ያለበት ሀቅ መሆኑን በግልጽ ለማሳወቅ እንወዳለን።

## ለተከበርከው ውድ የአማራ ሕዝብ ሆይ፡-

አንተ የነገደ አማራ ተወላጅ የሆንከው የአማራ ሕዝብ ከ1966 ጀምሮ ኢትዮጲያን ለመግዛት ስልጣን በያዙ ኋይሎች ሁሉ በነገዳዊ ማንነትህ እየተመረጥክ ከሌሎች ኢትዮጲያዊያን ብሔር ብሔረሰቦች እየተለየህ ይህ ቀረሽ እማይባል አሰቃቂ ጭፍጨፋ ፣አስተዳደራዊ በደልና አድሎዓዊነት በተከታታይ ሲፈጸምብህ እጅግ ታላቅ በሆነው ሆደ ሰፊነትህ፣ ሀገር አፍቃሪነትህና ታጋሽነትህ ችለህ ዝም ብትልም በ1983 ላይ ወደ ስልጣን የመጣው የትግራዩ ትህነግ ስልጣን መያዝ ጀምሮ ለሶስት አስርተ ዓመታት የተፈጸሙብህ ግፍ በደልና ጭፍጨፋ እጅግ አሰቃቂ የህነ ነው። ሆኖም በመጋቢት 2018 ላይ ወደ ስልጣን ከመጣው አቢይ አህመድ መራሹ የኦህዴድ ቡድን ለስልጣን መብቃት ወዲህ ላለፉት አምስት ዓመታት የተፈጸምብህ እጅግ ሰቅጣጭና አስቃቂ ጭፍጨፋ ግፍና በደል ላለፉት አርባና ሃምሳ ዓመታት የተፈጸሙብህን በሙሉ የሚያስከነዳ ጭፍጨፋን ነው እያስተናገድክ ያለህው።

አራት ኪሎ ላይ ስልጣን የያዘው የትህነግ ልጅ የሆነው ኦነጋዊው የኦህዴድ ብልጽግና በአማራ ግዛት ውስጥ ካለው ሌላው የትህነግ ስሪት ከሆነው የአማራ ብልጽግና ወይም ብአዴን ጋር በመሆን አንተን በነገዳዊ ማንነትህ ብቻ ለይተውና መርጠው መጥፋት ያለበት ነው በማለት መንግስታዊ የሆነ መጠነ ሰፊ የጭፍጨፋ ዘመቻ ተከፍቶብህ የአብራክህ ክፋይ በሆነው የአማራ ፋኖ ጭፍጨፋውን ሰብሮ ለማክሰም ከፍተኛ ትግልና መስዋእትነት እየከፈልክ ያለህ ሕዝብ ነህ።

ይህ በጉያህ የተወሸቀው ብዓዴናዊው ጸረ አማራ የትህነግ ስሪት ቡድን እና ኦነጋዊው የኦህዴድ ብልጽግና ባሕርዳር እና አዲስ አበባ አራት ኪሎ ላይ ስልጣን ይዘው እስከተቀመጡ ድረስ አንተ በአማራነትህ እየተመረጥክ መገደሉ መጭፍጨፉን እና ሀብት ንብረትህና እርስቶችህን መነጠቁን በስፋት ሲፈጸምብህ የምታይ ሕዝብ ትሆናለህ። ትናንት አማራው በወለጋ በመተከል በአርሲ ነጌሌ በሐረር በጉራፈርዳና በባሌ ሲጨፈጨፍ የምንሰማው ዜና ዛሬ አማራው አዲስ አበባ፣ ሰሜን ሸዋ ፣ወሎ፣ጎጃምና በጎንደር በየቤቱና በየደጃፉ ሲጨፈጨፍ የምንሰማበት የጨለመ ግዜ ላይ ነው የደረስነው።

ዛሬ አባይን ተሻግሮ በመጣው ኦነጋዊው የኦህዴድ ሰራዊት ጎጃም ምድር ላይ በደብረ ኤሊያስ ገዳም 557 መነኮሳትና መነኩሲት በግፍ ሲጨፈጨፉ የሰማንበትና ያየንበት፤ ዛሬ ዓባይን ተሻግሮ በመጣ ኦነጋዊው የኦህዴድ ሰራዊት በውስጣችን በተሰገሰጉ ብዓዴናዊያን ፊት መሪነትና አስተኳሽነት በጎንደር ጎርጎራ በወሎ ወልዲያ ቆቦ በሰሜን ሸዋ ሸዋሮቢት አጣዬ መንዝና አካባቢውና ብሎም በጎጃም በመራዊ በደምበጫ በሞጣና አካባቢው ላይ መጠነ ሰፊ የጭፍጨፋ ዘመቻ ተከፍቶ በሺህ የሚቆጠሩ አማራዊያን ሴቶች፣ህጻናት፣አቅመ ደካሞችና አርሶ አደሩ ሲጨፈጨፍ የሰማህበትና ያየህበት ወቅት ላይ ትገኛለህ።

ጸረ አማራ ዘመቻው መንግስታዊና ስርዓታዊ ከመሆኑ አንጻር ትህነግ የፈጠረው ሕገ መንግስት ተብዬ የሀገሪቱ መተዳደሪያ ሕግ እስከሆነና በዚህ ጸረ አማራ ሕገ መንግስት ሀገሪቷን የሚገዛ ኋይል አራት ኪሎ እስከተቀመጠ ድረስ የአንተ የነገደ አማራ ሕዝብ እድል እጣፈንታ ዘወትር መጨፍጨፍ ብቻ እና ብቻ ነው። ይህ በመሆኑም የአብራክህ ክፋይ የሆነው የአማራ ፋኖ እምቢ ብሎ በመነሳት

ለነገደ አማራ ህልውና በመታገል ላይ ነው። ጀግናውና አይበገሬው የአማራ ፋኖ በአጭር ግዜ ተጋድሎም እጅግ አስደናቂና አስደማሚ የትግል ጀብድ በመፈጸም የብልጽግናን ስርዓት እያንኮታኮተ ይገኛል።

እኛ በአውሮፓ በአፍሪካና በመካከለኛው ምስራቅ ያለን የነገደ አማራ ተወላጆችና ብሎም ኢትዮጲያዊያን በሙሉ ከዚህ ፍትሓዊ ከሆነው ከአማራ ፋኖ ሕዝባዊ ትግል ጎን ሙሉ በሙሉ የቆምን መሆናችንን ስንገልጽ በታላቅ ኩራትና በታላቅ ደስታ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን።

የአማራን ፋኖ ትግልንም በሙሉ ልባችን በእውቀት በዲፕሎማሲ በመረጃና በፕሮፖጋንዳ እና በሎጀስቲክስና በቁሳቁስ በመደገፍ ነገዳዊ ግዳታችንን ለመወጣት ወስነን መነሳታችንን ስንገልጽ አንተ ታላቁ የአማራ ሕዝብ ደግሞ ይህንን ታሪካዊና ወሳኝ የትግል ሁኔታን በድል ለመደምደም ትንሽ ሳትል ትልቅ ሴት ሳትል ወንድ አማራ የሆንክ ሁሉ ፋኖን በመቀላቀል የተፍረከረከውን ፋሺስታዊ የብልጽግናን ስርዓት ላንዴና ለመጨረሻ ግዜ መንግለህ በመጣል ነጻነትህን የምትቀዳጅ ትሆን ዘንድ ጥብቅ ጥሪን በማቅረብ ነው።

## ለመከላከያ ሰራዊት አባላት፡-

ወዳችሁም ይሁን ተገዳችሁ በአማራ ሕዝብ ላይ ቃታ እየሰባችሁ ላላችሁ የመከላከያ ሰራዊት አባላት በሙሉ ድርጊታችሁን በጥብቅ እናወግዛለን። የሀገር መከላከያ ሰራዊት ከተቋቋመበት የአንድን ሀገር ሉዓላዊ ግዛት ዳር ድንበር ከወራሪ ጠላት የመከላከል ተግባርና ግዴታ ውጪ በሕዝባችሁ ላይ ተሰማርታችሁ ለምታደርጉትና እስከዛሬም ላደረጋችሁት ጭፍጨፋ ሙሉ በሙሉ ተጠያቂ መሆናችሁን በመግለጽ ድርጊታችሁን እጅግ አጥብቀን እናወግዛለን።

ስለሆነም እናንተ የአንድ ሀገር መከላከያ ሰራዊት እንጂ የአንድ ፋሺስታዊው የኦህዴድ/ብዓዴን ድርጅት ጉዳይ አስፈጻሚ ስላልሆናችሁ አሁንም ቢሆን በአስቸኳይ ከአማራ ግዛት ለቃችሁ በመውጣት ወደ ካምፓችሁ እንድትገቡ አጥብቀን እንጠይቃለን።

ይህንን ሳታደርጉ ቀርታችሁ የኦህዴድ መጠቀሚያ በመሆን በሕዝባችን ላይ ቃት ለምትስቡ ግን በያላችሁበት እያደንን እናንተን ለፍርድ የምናቀርብ መሆናችንን እንድታውቁ እንወዳለን። መቼም ቢሆን የአማራን ደም አፍሥሶ በሰላም የሚኖር አንድም ኋይል እንደማያመልጠን ዛሬ ላይ ሆነን በጥብቅ ልናስጠነቅቅ እንወዳለን።

## በዳያስፖራ ለምትኖሩ የአማራ ተወላጆች፡-

በዳያስፖራ ላለህው የነገደ አማራ ተወላጅ በሙሉ የምናስተላልፈው ጥብቅ ጥሪ መላው የአማራ ዳያስፖራ አትኩሮቱን ሁሉ በሀገሩ ላይ በማድረግ ነገዳዊ ግዴታውን እንዲወጣ እና ለዚህም ሁላችንም በጋራና በአንድነት እንድንቆም ጥብቅ ጥሪ ስናስተላልፍ በእኛ በኩል ከሁሉም ጋር አብሮ ለመስራትና ብሎም ለማስተባበር ሙሉ በሙሉ ዝግጁነታችንን በይፋ በመግለጽ ነው። ስለዚህ በድህረ ገፃችን ላይ የሚገኘውን ፎርም ሞልተው አባል ይሁኑ:: www.amharafano.org

ዛሬ እኛ ካልተባበርን አማራዊ አንድነትን ካልገነባን መች እንተባበራለን?

## ሕልውናችንን በክንዳችን እናስጠብቃለን! ድል ለአማራ ፋኖ ! ድል ለታላቁ አማራ ሕዝብ!

የኢትዮጲያዊያን ማሕበር በአውሮፓ
የአማራ ማሕበር በሀገረ እንግሊዝ
ኢትዮ ጀርመን ግብረሃይል
አማራ ማህበር ሆላንድ
አማራ ማህበር ቤልጅየም
አማራ አንድነት ስዊድን
ኢትዮ አማራ ኖርዌይ
አማራ ፋኖ ደጋፊዎች ስፔን
የአማራ ግሩፕ አውስትሪያ
አማራ ህብረት አየርላንድ
አማራ ትብብር ስዊዘርላንድ
ማማ ሚዲያ
ጋሻ ሚዲያ